# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 3 ቁጥር 7 — ግንቦት 20 ቀን 2011 ዓ.ም.


## የ28 ዓመቱ የ100 ዓመት የቤት ሥራ

*የድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ (https://www.youtube.com/watch?v=kld8S_T-Fok&feature=youtu.be)*

የሰሞኑ የአዲስ አበባ መብራት በፈረቃ ጉዳይ ሀገር ወዴት እየተጓዘች ነው? ቢያስኝ አያስደንቅም። ገጠሩ የሀገራችን ክፍል እንደሆነ ተለማምደውታልና ላምባቸውን ተማምነው ይኖራሉ። መብራት የለም፣ ውሃ ሄዳለች፣ የዶላር ምንዛሪ እጥረት ገጥሞናል፣ አቤት! ቆሻሻ፣ ዳቦ አምስት ብር ገባ፣ ለተፈናቀሉ ዕርዳታ፣ መንግሥት ይድረስልን፣ የደሞዝ ጭማሪ ያስፈልገናል፣ ትምህርት አቋመናል፣ አምስት ሚልዮን ለእራት፣ የማንነታችን ጥያቄ ምላሽ አሁኑኑ፣ ዘራፊዎችን በቁጥጥር ሥር አደረግን፣ ምኒልክ ትምህርት ቤት ለፈርስ ነው ሌላም ሌላ እየሩን ከሞሉት ዜናዎች ጥቂቶቹ ናቸው።

ኢትዮጵያ በአለፉት 28 ዓመታት እንደ መንግሥትና ብድር አጉራፊ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እናስብ ካልን በዓመት በአማካይ 11 ከመቶ ዕድገት አሳይታለች። እንደ ሀገር፣ እንደ ሕዝብ፣ ምድር ላይ ስለሚራመደው ሃቅ ካሰብን በቀን ሦስቴ መመገብ ያቃተው ሕብረተሰብ በ28 ዓመት ጉዞው ያተረፈው ቢኖር "ቁምሳ" (ቁርስ ምሳ እና እራት አጣምሮ በቀን አንዴ መመገብ የፈጠረው ቃላት) ነው። ኢትዮጵያ በትንሹ የ15 ዓመት የምጣኔ ሃብት ጉዞዋን ብንመለከት በአማካይ የ16ብር አንድ ኪሎ ሥጋ ዛሬ 350 ብር ዕድገት ያሳየበት፣ የአንድ ኩንታል 400 ብር  የጤፍ ዋጋ ዛሬ 2000 ብር የሚሸመትበት፣ የ200 አንድ ፈረሱላ በርበሬ 1000 ሺህ ብር እድገት ያሳየበት በጥቅሉ ከምግባ ምግብ ጥራጥሬው፣ አትክልቱ፣ ፍራፍሬው እንዲሁም ዘይት፣ ሽንኩርት፣ ድንች፣ ዶሮ፣ እንቁላሉ፣ ከብቱ ለጆሮ በሚዘገንን ሁኔታ ያሻቀበበትን ዘመን ዕድገት ካልነው አነጋገራችን የተገላቢጦሽ ሁኗል ብንል አግባብነት ይኖረዋል። በእነኚህ መሠረታዊ የምግብ አቅርቦት ላይ ያለው እጥረትና የዋጋ ግሽበት ሌላውንም ይነካዋል። የጨርቃ ጨርቅ ዋጋ፣ የግንባታ ዕቃዎች፣ መድሐኒት፣ የትምህርት ቤት ቁሳቁሶች፣ የቢሮ መገልገያዎች እንዴት እንደሚንሩ መገመት አያዳግትም። ከትላልቅ ነጋዴዎች ጀምሮ ለዕለት ጉርሳቸው በጉልትና በሱቅ በደረቴ ከሚቸረችሩት ድረስ በከፍተኛ ዋጋ ገዝተው ያመጡትን ሲቸረችሩ የበደሉ ክምር ተሸካሚ ሕዝባችን ላይ ይጨምሩለታል፣ ወቸው ጉድ! ያሰኙታል። በችርቻሮ ዕቃዎች ላይ ያለው የዋጋ ጭማሪ አሁን አሁን የየዕለት በመሆኑ ሕዝባችን ከመገረም አልፎ ምን እንደሚመጣ ተመልካች ከሆነ ሰነባብተዋል።

በየቤቱ ካለው ሚላስ ሚቀመስ እጥረትና አለመኖር የተነሳ የዛሬ ሕፃናት የነገ ሀገር ተረካቢዎች ወደ ልመና፣ ቆሎ/የተቀቀለ ድንች አዟሪነት፣ ሎተሪ አዟሪ፣ ጫማ ጠራጊ/ሊስትሮ፣ ሴተኛ አዳሪ ወዘተ በመሆን እራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ቤተሰባቸውን የሚያቃምሱ በርካታ የቤተሰብ አካላት በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ከተሞች ጎልተው ይስተዋላሉ።

*ቀን ሙቀቱን ሌት ብርዱን በባዶ ሆድ መቋቋም የተሳናቸው የጎዳና ተዳዳሪ ወገኖቻችን በመጠጡ፣ ሲጃራው፣ ጫቱ፣ ሀሽሹ፣ የመኪና ጋዝ ሽታ እራሳቸውን አደንዝዘው ቀን የሚቆጥሩ ሕፃናትና ወጣቶችን ብዛት ለተመለከተ የዚህ ቁጣ መጨረሻው ምን ይሆን? ከማለት አልፎ በዚህ መልኩ ያለፈ ትውልድ ነገ ዕድላቸው ምን እንደሚሆን ለመተንበይ አስቸጋሪ አይደለም።*

*አዲስ አበባ መሸከም ከምትችለው አቅም በላይ በመጨናነቅዋ በቤት ኪራይ ክፍያ የሚሰቃየው የመንግሥት ሠራተኛ በቀን አንዴ በልቶ ደሞዙን ያስረክባል። ትዳርና ልጅ ሲቀላቀሉበት ልጅም በድሉ ያድጋል፣ ትዳሩም ይቀጥላል። በከተማዋ ከሚታየው ሕዝብ ብዛትና የትራንስፖርት አቅርቦት ታክሲ፣ ውይይት፣ ባጃጅ፣ አውቶቡስ፣ በቅርቡ ግልጋሎት መስጠት የጀመረው የከተማ ውስጥ ባቡር አለመመጣጠን አንጻር ወደ ሥራ እና የተለያዩ ጉዳዮች ለመጓዝ የሚወጣው ነዋሪ እየተፈራረቀ ባለው ጠራራ ፀሓይና ሃይለኛ ዝናብ ረዥም ሠልፍ ቁመው የሚጠባበቁትን ወገኖች ማየት የ28 ዓመቱ ዕድገት ውጤት ነው።*

*የገጠሬውና የገጠር ከተሞች የኑሮ ውድነትና የሰቀቀን ኑሮ ዛሬ ባልተለመደ ሁኔታ ሳይወዱ በግድ ወደ አዲስ አበባ የሚፈልሰውን ቁጥር እጅጉን አግዝፎታል። ተለምኖም፣ ተሰርቶም፣ የሚገኘው አዲስ አበባ ነውና። ሕይወት ተኩኖ ኑሮን ለማሸነፍ ስርቆትም ዛሬ ሥራ ሁኗል። ማጅራት መቺው፣ ኪስ አውላቂው፣ ቁጭ በሉ፣ ጉቦኛው፣ የመንግሥት ካዝና ዘራፊው፣ አየር ባየር ነጋዴው፣ ባንክ ባበደረ የደስ ደስ ተቀባዩ፣ ፖለቲከኛ በተኮነ ኮንደሚንየም ተረካቢው፣ ተዘርዝሮ የማያልቅ የዘረፋ ዓይነት በመንግሥት ደረጃ የተለመደና የሕይወት ዘርፍ ተደርጎ ከተወሰደ እነሆ 28 ዓመት አስቆጠረ።*

*ችግሩ ያለው እውነቱን ሃቁን ስንነጋገር ነው። ወቅታዊ የሀገራችንን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ችግሮች ስናነሳና ስንዳስ ዳር ዳሩን ስለማንጓዝ የሚያኮርፉ ቢኖሩም እንቀበላለን። የምንናገረው ፍዳውን እያየ ስላለው ሕዝባችንና ምስኦዋ አዝምሞ መውደቂያዋ ለተቃረበው ጎጃችን ጉዳይ ነው። ሲያነዱ እየነደደች፣ ሲያጤሱ እየጤሰች ያለች የመሰለችው ጎጆአችን ዛሬ የገጠማትን መሠረታዊ የኑሮ ውድቀት ለመመከት ምን ማድረግ እንዳለብን ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶትና በፖሊሲ ደረጃ ተቀርጾው ተግባርዊ ሊደረጉ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችን ችላ ካልናቸው አወዳደቃችን አስከፊ ይሆናል።*

*ከደኖቿ ስፋት፣ ከወንዞቿ ብዛት፣ ከጋማና የቀንድ ከብቶቿ ብዛት፣ ከምድሯ ለምነት አንፃር፣ የት መድረስ የሚገባት ኢትዮጵያችን ምን ቢያጋጥማት ነው ቁልቁል እየወረደች ያለችው? ልጆቿን መመገብ ምነዋ ተሳናት? ሊታይ የሚገባው አሳሳቢ ጉዳይ ነው። በዛሬ መነጽር ስንመለከት ደግሞ ደኖቿ ወድመዋል፣ ምድረ በዳነቷ እየሰፋ መጥቷል፣ ወንዞቿ ደርቀዋል፣ ያልደረቁትም መጠናቸው እጅጉን ቀንሷል፣ አፈሯ ለምነቱን አጥቷል፣ እየተሸረሸረም አልቋል ለምን? ከገጠማት መንግሥታዊ አስተዳደር ጀምሮ፣ ተፈጥሮን አስታኮ፣ ዓለም አቀፍ ዕርዳታ ሰጪዎችን አሳቦ፣ ዘራፊ ሌቦችንና ሙሰኞችን ጨምሮ ምክንያት እየደረደሩ ጥናታዊ መረጃ ማቅረብ ይቻላል። ግና መፍትሄው ምን እናድርግ? የቀድሞውና የአሁኑ ትውልድ "የረሃብ" ትውልድ ሆኖ እንደተጓዘ መቀጠሉ ይቅርና ለመጪው ትውልድና ለሀገር ዛሬ ካላሰብን ኢትዮጵያችን እያሉ እንደሌሉ ከሚቆጠሩ ሀገሮች ተርታ እንዳትገባ ሊያሰጋን፣ ሊከነክነን ይገባል።*

*ኢትዮጵያችንን በአሁኑ ወቅት ቀስፈው የያዟት ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች በሰይፍ ስለት ጠርዝ ላይ እንዳለች መታወቅ አለበት። የሚቀጥሉትን ጥቂት ዓመታት ከዚህ አደጋ ለመውጣት ወይም ለመሠየፍ ወሳኝ ናቸው።*

በዓፄ ኃይለሥላሴ ዘመን 1966 ዓ.ም. አብዮትን መነሻ ብናደርግ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ወደ 25 ሚልዮን አካባቢ ነበር። በዚህ 45 ዓመት በአሁኑ ወቅት 110 ሚልዮን ይገመታል። ይህ ማለት የሕዝብ ብዛታችን በዓመት 2.5 ሚልዮን ይጨምራል ማለት ነው። በዚህ ከቀጠለና አሁን ያለንበትን የኢኮኖሚ ችግር መቅረፍ ካልቻልን አሁን ያለነው ትውልድ ለሀገር ውድቀትን አስረክበን እንደምንሄድ ልንጠቁም እንወዳለን።

አውሮፓና ያደጉት ሀገራት የሕዝብ ቁጥር መጨመርን ትኩረት ሰጥተው በመቀነሳቸውና ለዕድገትና ለልማት በሚያመቻቸው ጎዳና መንቀሳቀሳቸው ዛሬ ለደረሱበት የሥልጣኔ ደረጃ አብቅቷቸዋል። ትላንት አልፎብናል፤ ዛሬም ቆሞ አይጠብቀንም፤ ኢትዮጵያን ከውድቀት አድነን ለተተኪው ትውልድ እናዘጋጅ ካልን በመንግሥት ደረጃ ፖሊሲ ተቀርጾለት በየዓመቱ የሚጨምረውን የሕዝብ ብዛት በመቀነስና ተዛማጅ የምጣኔ ሀብት ዕድገት ማምጣት ካልተቻለ ከአለው ብልሹ አስተዳደር ላይ መከራና ችግር እየጨመርን መሆናችንን ልንገነዘብ ይገባል። ኢትዮጵያ የእምነት ቃል ኪዳን ሀገር እንደመሆኗ የእምነት ተቋማትን አስተባብሮ ስለ ቤተሰብ ምጠናና ስለመሳሰሉት በፖሊሲ ደረጃ ዕቅድ ወጥቶ መራመድ ካልቻልን ከአለው የዘረኝነት ፖለቲካ ጋር ተዳምሮ ለሀገራችን ከፊታችን የተደቀነው ዕድገት ሳይሆን ውድቀት መሆኑን ጅማሮውን እያየን ነው።

ኢትዮጵያ ዛሬ በርካታ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ አንገብጋቢ ጉዳዮች ከፊቷ ተደቅኗል። ይህንንም መጠነ ሰፊ ችግሯን ለመፍታት በቅድሚያ ለሀገርና ሕዝብ ተቆርቋሪና አሳቢ አገዛዝ ያስፈልጋታል። ፖለቲካውና ኢኮኖሚው እንደማይነጣጠሉ ሁሉ በዘርና ቋንቋ የተካለለና የተቧደነ አገዛዝ ሀገርን ከውድቀት አያድንምና ሀገር እንድትቆም ሀገር አፍቃሪ፣ ሰንደቅ ዓላማዋን አክባሪ፣ ሕዝቧን ሳያበላልጥ ወዳድ፣ የግለሰብን መብት አክብሮ አስከባሪ፣ በወረቀት ሳይሆን በተግባር ከሕግ በታች ያለ አገዛዝ ደግመን ደጋግመን እንዳልነው ዛሬ ላነሳነው የሀገራችን ምጣኔ ሀብት ድቀት መፍትሄ ሰጪ ነውና ልንጠቁም እንወዳለን። ልማት በሀገር ደረጃ ሲሆን ለኢትዮጵያዬ ተብሎ ብሔራዊ ግዴታን ሁሉም ይወጣል፤ በሌላ በኩል ልማት በክልል ከሆነ ሌላውን አግላይ ብቻ ሳይሆን በክልሉ አይመለከቱኝም የሚላቸውንም የህብረተሰብ ክፍሎች ወደ ጎን መግፋቱ አይቀሬ ነውና ዕድገቱ ውድቀት እንደሆነ ከ28 የኢሕአዴግ አገዛዝ አይተናል።

ኢትዮጵያ በፖለቲካውም፣ በኢኮኖሚውም፣ በማህበረሰባዊ ጉዳዮችም የሀገር ሉዓላዊነቷንና የሕዝቧን አንድነት አስጠብቃ ወደ ልማትና ዕድገት ጎዳና እንድታመራ ከተፈለገ ያለምንም ጥርጥር ሥር ነቀል ለውጥ ያስፈልጋታል። በአጭሩ ፍርጥርጥና ዘርዘር አድርገን ለማስቀመጥ የኢሕአዴግ/ህወሓት/ኦዴፓ አገዛዝ ከነሕገ መንግሥቱ ማብቃት ይኖርበታል። የአንድ ዓመቱን የጥገና ጉዞ በ“ለውጥ” ስም ስንገመግመው የሀገሪቷን የእርስ በርስ ግጭት አፋጠነው፣ በገንጣይ ሕገ መንግሥቱ መሠረት የማንነት ጥያቄን አጋጋለው፣ በአንፃራዊነትም ቢሆን ይንቀሳቀስ የነበረውን የነጋዴ ህብረተሰብ አሽመደመደው፣ የሕዝቡን የኑሮ ውድነት ከቀን ወደ ቀን የትዬ ለሌ አጦዘው፣ የህብረተሰባችንን የቀን ተቀን እንቅሳቅሴ ሰቀቀን እንዲውጠው አደረገው፣ ቋጨት ስናደርገው የቀን ጅቦች ወደ ማታ ተቀየሩ እንጂ ሌብነቱ ቀጥሏል።

በመሆኑም ችግሩ ያለው የተበላሸው አገዛዝ ላይ ነው። በሌብነት የተካነ ቢሮክራሲ ለውጥ ሊያመጣ አይችልም። ሀገር በልመና ከድህነት አዘቅት ልትወጣ አትችልም። ለጋሾቻችንም ለእኛ ሰጥተው ማንነታችንን ጨምረው ሀገራችንን እየወሰዱና በእነሱ ቁጥጥር ሥር በማድረግ አፍሪካን ጨምሮ ዳግም የሸቀጣቸው ማራገፊያ በማድረግና ያለንን የተፈጥሮ ጸጋ ለመጠቀም ከተንደረደሩበት ዓለም አቀፋዊ

የምጣኔ ሀብት ዘረፋ እቅዳቸው መጠቀሚያ ቢያደርጉን ጥፋቱ የራሳችን ነውና ልናዝን አይገባም። ያልነበረብንን ዓመል እጃችንን አጣጥፈን ዛሬ ባዕዳንን እንመለከታለንና።

የሰሞኑ አዲስ አበባን የማስዋብ ዜና ማንም አይጠላውም፤ "ፊንፊኔ ኬኛ" ባዮችም ተውባ "ቢረከቧት" ይመርጣሉ። እውን ግና አዲስ አበባ ለምን ለዚህ በቃች? ለአንድ ከተማ መቆርቆር ዋና መሠረት የከተማዋ ፍሳሽ፣ ቆሻሻ ተፈጥሮአዊ ውበቷን እጅጉን ሳያዛባ በባለሙያ ተጠንቶ በሚገነቡ ቤቶች፣ ሕንጻዎች፣ ፋብሪካዎች፣ ሆቴሎች፣ መሥሪያ ቤቶች ወዘተ ተፋሰሶች የከተማዋን ማስተር ፕላን አካቶ መካተት ሲገባው ከጅምሩ አልተደረገም። የከተማዋ የሽንት ቤት ተፋሰሶች ወደ አቅራቢያ ግልገል/ገባር ወንዞች ይገባሉ። ሌላም ሌላ ዝቃጮችና ቆሻሻዎች እንዲሁ። ይህ ጉዳይ ከሙያ አንጻር አንድን ወንዝ ብቻ ሳይሆን ገባር ወዞችንም ይመለከታል። በተጨማሪ የከተማዋ ማስተር ፕላን ከተፋሰሷ ጋር ተዳምሮ የኤሌክትሪክ፣ የስልክ መስመሮችን እንዲሁም የውሃ ቱቦዎችን ያካተተ ሰፊና መሠረታዊ ጥናትና ዕቅድ ሊደረግበት ሲገባ ነጥሎ አንድን አካባቢ ለማስዋብ በሚደረግ መጠጋገን የከተማዋን አጠቃላይ ችግር ሊቀርፍ አይችልም።

አዲስ አበባን የማስዋብ ዕቅድ ቅድሚያ የሚሰጠው አይደለም ስንል በቅድሚያ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በጎዳናዋ ላይ ከቆሻሻ እየተመገቡ፣ ቆሻሻ መኝታቸው ለሆኑ ዜጎቻችንን ማየትና መጠለያ መስጠት ይገባልና ነው። በየመንገዱ የተከመሩት ከየቤቱና ከሌላም የሚወጡት ቆሻሻዎች በአግባቡ በየአካባቢውና በየመንደሩ የሚነሱበትንና ወደፊትም በአግባቡ ከየቤቱ እየተሰበሰቡ ከከተማዋ ውጭ የሚከማችበት መንገድ መታቀድ ይኖርበታል። ወደ ወንዝ የሚጣሉ ቆሻሻዎችና ፍሳሾች እንዴት ተቀባይ ይኑራቸው? ቀዳሚ ውጥን መሆን ይገባዋል። ከዚህ በፊት "ኦሮሚያ በክልሉ" የአዲስ አበባ ቆሻሻ አይከማችም በሚል ያስቆመው ሂደት የዘር አከላለል ያመጣው ጣጣ በመሆኑ ነው። ይህ ካላበቃ አዲስ አበባም አትጸዳም ሌላውም አይለማም። የአንድ ከተማም ሆነ አካባቢ እድገትና ልማት ከሌላው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተያያዘ ነውና። አዲስ አበባም ሆነች ሌሎች ከተሞች በየትኛውም የሀገሪቷ ክፍል ባለሙያዎች የቆሻሻ ማከማቻ በመደቡት ሊተገበር ይገባዋል። ይህ የሚሆነው ግና የአዲስ አበባም ሆነ የሌላው ልማታችን ለሀገር መሆኑን ስንቀበል ነው።

ከተማዋን በከበቡት ተራራዎች እንጦጦ፣ ጉለሌ፣ የካ የመሳሰሉት ዛፎቿ ተመናምነው ባዷቸውን ቀርተዋል። እነኚህ ዛፎች ዳግም ችምችም የሚሉበትንና ለከተማዋ የአየር ፀባይና የከርሰ ምድር ውሃ ማጠራቀሚያነት ተፈጥሮአዊ አስተዋጽዖአቸውን ያበረክቱ ዘንድ ቅድሚያ የደን ተከላና እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል። የዘር ፖለቲካ ያመጣው ጣጣ ያፈናቀላቸውን ወገኖቻችንን የመፈናቀሉ ውጤት በምግብ፣ በጤና፣ በሥራ፣ በትምህርት በማህበረሰባዊ ሕይወት የፈጠረባቸውን መቅረፍ ሲገባ በተንሳቆለ ህብረተሰብ ላይ ስለ ውበት መስበክ ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ያስገኛል ተብሎ ከሆነ የዋህነት ወይም ችግሩን በቅጡ ሳይረዱ ለስምና ዝና የሚደረግ ጥረት ነው።

ሌላው የሰሞኑ ዜና መብራት በፈረቃ ነው። እያንዳንዱ አካባቢ ከተመደበው የ24 ሰዓት ሦስት ፈረቃ አንዱን ከመብራት ይገላገላል ማለት ነው። ይህ ደግሞ በቅርቡ በእጥፍ የተጨመረው የመብራት አገልግሎት ክፍያ በተጨማሪ ነው። ጨለማም ቢሆን የቆጣሪው ታሪፍ አይቀንስም። የመብራት ኃይል ባለስልጣኑ ችግሬን ለመቅረፍ ሕዝቡ የታሪፍ ጭማሪውን በመቀበል ይተባበረኝ፤ ይህ ካልሆነ መንቀሳቀሻ የለኝም ሲል ለፈረቃውም የግድቦቹን ውሃ ማነስ ምክንያት ሰጥቶ ድምጽ አልባ ተፈጥሮዎች ላይ ያላክካል። ይህ ሁሉ የ28 ዓመት ዘረፋና ሌብነትን ጨምሮ ሀገር ጠላቱ ከሆነችበት ወያኔ/ኢሕአዴግ ሥልጣን ሲይዙ ሊሠጠን የተፎከረብን የመቶ ዓመት የቤት ሥራ አካል ነው።

መብራት በፈረቃ ቀጣይነት ምርት በፈረቃ፣ ሕክምና በፈረቃ፣ ንግድ በፈረቃ፣ ሕይወት በፈረቃ ይህን ለመቅረፍ መረባረብ ሲገባ አዲስ አበባን እናስውብ ተውኔት ይካሄዳል።

አዲስ አበባ ችግሯ ተፋሰስ ወንዞቿ ብቻ አይደሉም፤ ይህች ሰፊ ከተማ ጉራንጉሯ ሲቃኝ ስንት ጉድ ተሸክማለች። የሰው ልጅ ይህን ሁሉ ይችላል ታሰኛለች። የመንደር መንገዶች ያቆሩት ውሃ ከተማዋን የወባ ትንኝ መናኸሪያ አድርጓታል። ይህ ደግሞ በቀጣይነት መረጃው ባይኖረንም በአዲስ አበባ በወባ በሽታ ተጠቂው ከዚያው ከከተማይቱ እንደሚነሳ መተንበይ ቀላል ነው። እና! የቱሪስት መስህቦ እናስገኝላት የተባለችው አዲስ አበባ ጎብኚዎቿ በሽታ ለመሸመት ይመጡልናል ብሎ ማሰብ ቅዠት ይሆናል።

ቀደም ሲል ያለ ዕቅድ የተጀመሩ ማለትም የኢትዮጵያን መሠረታዊ ችግሮች ያላገናዘቡ ፖሊሲዎች፣ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተብለው በተግባር ብዙ ገንዘብና የሰው ኃይል ያባከኑ ፕሮጀክቶች ናቸው። በአምስት ዓመት ይጠናቀቃል ተብሎ አንጀራ ጋጋሪ፣ ጉልት ቸርቻሪ የመሳሰሉትን ምስኪን እናቶችን ሳይቀር ከመቀነታቸው ሳንቲማቸውን የለቀመው ዕዳሴ ግድብን ጨምሮ ሌሎች ለዚህ ምሳሌ ናቸው። ከዚህም አልፎ የዕድገት ተምሳሌት ይመስል በብድር የተመሠረተው ኢኮኖሚ ከዓለም ፈጣን ዕድገት አስመዝግቧል እየተባለ ኢትዮጵያችንም ከመካከለኛ ገቢ ሀገሮች የማሰለፍ ባዶ ተስፋ ምን ያህል ዋና ዋና መሠረታዊ የኢትዮጵያችንን ችግሮች አለመረዳትና በማጭበርበር የሥልጣን ዕድሜን ለማራዘም እንደሆነ አሁን ግልጽ ሁኗል።

በጥቅሉ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከፖለቲካው ባሻገር ከፍተኛ የኢኮኖሚ ውድቀት ላይ ገብታለች። በዶላር ምንዛሪ እጥረት የተነሳ የአስመጪና ላኪ እንቅስቃሴው ተሽመድምዷል። ነጋዴዎች ቤት ኪራይና የሠራተኞች ደሞዝ በመክፈል ከተቀመጡ ወራትን አስቆጥረዋል። መንግሥት እንኳን ደሞዝ ሊጨምር ለሚከፍለውም ግራ ተጋብቷል። አዎ የመንግሥት ሠራተኛውን ኑሮና ውሎ ለተመለከተ ሀገሪቷ ከገባችበት ውድቀትና የኑሮ ውድነት አንጻር በእጥፍ እንኳ ቢጨመርለት አመርቂ አይደለምና መፍሄው “መቻል ነው” እንዳንል ጭካኔ ነው። የቀን ጅቦች ተብለው ስም የወጣላቸው ዘራፊዎች በቢልዮን የሚቆጠር የሀገር ገንዘብና ሀብት ዝርፊያቸው ስም በማውጣት ብቻ ዝም መባሉን ሳንዘነጋ ለማስመለስና በመጠኑም ቢሆን ለአንዳንድ ችግሮች መቅረፊያ አለመታሰቡና በዝምታ መታለፉ የአንድ ሰሞን ድጋፍ ማግኛ እንደነበር ዛሬ ብንናገር እንጼታ! ያሰኛል።

ኢትዮጵያ ሀገራችን በፖለቲካው ወድቃለች፣ በኢኮኖሚው አዘቅት ወርዳለች፣ በማህበራዊ ሕይወቷ ተመሰቃቅላለች። ለዚህ ሁሉ ቀውስ ሲፈጠሩም ኢትዮጵያን ለማዳከም ተጠንሠው ሥልጣን ሲይዙም ሰንደቅ ዓላማችንን ጨርቅ ብለው ያራከሱ፣ ታሪካዊ ቅርሶቻችንና ሀውልታችንን ድንጋይ ብለው ያጣጣሉ፣ አሰብ ወደባችንን የግመል መጠጫ በሚል የሸጡ፣ ትውልዳችንን የቀበሩ ሌላም ሌላ የሠጡን የ100 ዓመት የቤት ሥራ እውነትም ሰምሮላቸዋል። በዚህ 28 ዓመት አገዛዛቸው በሀገራችንና በሕዝባችን የሰነቀሩብንን መከራና ስቃይ ለመወጣት እውን ከባድ ሸክም ጥለውብናል። የተሠጠንን የቤት ሥራ የምንሠራው ለሀገርና ለሕዝብ ተቆርቋሪ መንግሥት ሀገራችን ካገኘች ብቻ ነው።

በ“***አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***” ተደጋጋሚ አባባል አሁን ያለው የኢሕአዴግ አገዛዝ ተጨማሪ የቤት ሥራ ይሰጠናል እንጂ መሠረታዊ ለውጥ አያመጣም። አንዳንድ ቅን አሳቢዎች እውነትም አሁንም አቅሙ ካላቸው ይህ አገዛዝ 28 ዓመት በሀገሪቷና ሕዝባችን ላይ ላደረሰው ውድቀት እራሱን ተጠያቂ አድርጎ ሀገሪቷን ለሽግግር መንግሥት ማስረከብ ይኖርበታል። ይህ እስካልሆነ አገሪቷ ወደ እርስ በርስ ግጭት እያጋደለች ሲሆን በሌላ በኩልም የደረሰባት ኢኮኖሚያዊ አዘቅት ውድቀቷን አፋጥኖ አሳዛኝና ዘግናኝ ጥፋት እንዳይከሰት ጊዜውን እንጠቀምበት

**እንላለን። በደካማ ጎናችንና በውድቀታችን ተጠቅመው ሀገሪቷ ተበታተነች፣ ሕዝብ አለቀ ደንታ ለሌላቸው የቀን ጅቦች ሳይሆን የቀን ገዳዮች ሀገሪቷን አሳልፈን አንሰጥ ስንል ድምጻችንን እናሰማለን። ለዚህም የተቀነባበረ ሕዝባዊ ትግላችን ይቀጥል እንላለን።**

**ሥር ነቀል ለውጥ ኢትዮጵያን ለማዳን!**
**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!**

**"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"**

**ግንቦት** 20 **ቀን** 2011 **ዓ.ም.** (May 27, 2019)

**በ**1964 **ዓ.ም. የተጻፈውንና ዛሬም ህያውነት ያለውን**
**የገጣሚ፣ ደራሲ፣ ሃያሲና የሥነ ጽሁፍ ተመራማሪ ደበበ ሰይፉ ግጥም**
**"እማማ እማማዬ" በቀጣዩ ገጽ ይመልከቱ።**

<u>ማሳሰቢያ ፡</u>

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «***ኢትዮጵያችን***» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ስልክ፡ **703 300 4302**
ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin

## እማማ...እማማዬ

እማማ እማማዬ...
የኄነት መደብ መብቀያዬ
የኄነት መደብ አሻራዬ፤
እስቲ ፡ እንምከር እንወያይ
ገበናሽ ገበናዬ
ተፈልቅቆ እየታዬ።

ከማሕፀንሽ እምባ በቅዬ
መልክ ስምሽን ከመልክ ከስሜ አንጠልጥዬ
ግርማ ሞገስሽን ተካፍዬ
ያለውለታዬ፤
ስሐሽን ተቀብዬ
ያለዕዳዬ፤
ዕድልሽ ከዕድሌ ተቆራኝቶ
ገነቴ በገነትሽ ተመስርቶ
ፍዳዬም ከፍዳሽ ተጋርቶ፤
ምነው ታድያን ቆይቶ ይታየኝ ጀመር ተለያይቶ
ያዋደደን ገመድ ተፈቶ
ውጥሩ ረግቦና ላልቶ?
ምንድን ሆነ እማምዬ ፡ በማኻላችን ምን ነፈሰ
ቃልሽን ከቃሌ ያበሰ ፡ ውላችንን ያፋለሰ
ገጽሽን ከዐይኔ የገሠሠ
ምንድን ሆነ እማዬ ሆይ ፡ በማኻላችን ምን ነፈሰ?

ብትጠሪኝ እንዳልመልስሽ
ብትልኪኝ እንዳልላክሽ
ፊቴን አዙሬ እንዳልፍሽ
ብትቀርቢኝ እንድርቅሽ
ብታወሪ እንዳላዳምጥሽ
ብትጽፊ እንዳላነብሽ
ውሸት ብዬ እንድሥቅብሽ
ተረት ብዬ እንዳገጥብሽ
ያደረግ ፡ ምንድን መዓት ተተኮሰ
ምንድን ሆነ እማምዬ ፡ በመኻላችን ምን ነፈሰ?
ቃልሽን ከቃሌ ያበሰ ፡ ውላችንን ያፋለሰ
ገጽሽን ከዐይኔ የገሠሠ
ምንድን ሆነ እማዬ ሆይ ፡ በመኻላችን ምን ነፈሰ?

እባክሽ ፡ ዘራችን በውል ይታወቅ
በወግ ይቆጠር አይደበቅ
በመጤ ተረብ አይታመቅ
በባዕዳን ክርን አይድቀቅ፤
እኔና አንቺን እሚያውቀን
የታሪክ ልሣን ይፍረደን ፡
ሲይዙኝ በጠይምነቴ
ፀሐይዋ አትሁን ምክንያቴ።

እማማዬ ፡
ከዶቃው ጋር ከአፈሩ
ከዳዬው ጋር ከእሹሩሩ
ከሕመሙ ከጭንቀቱ
ከቡረቃው ከሐሴቱ
ከበጋው ጋር ከክረምቱ
ከብርዱ ጋር ከሙቀቱ
የነበርሽ - የተካፈልሽ ፡
አሁን ወዴት ይሆን ያለሽ?
በይ ፡ አምባሻ የለሽም ወይ ዳቦ
ጨጨብሳ የለሽም ወይ ጭኮ
ጐመን ፡ የለሽም ወይ ገንፎ፤
ያንቺን ገበታ ደፍቼ
ጽዋሽን በእጆቼ አንክቼ
የባዕድ ማዕድ ስመጥን
ወጥሽ ሻግቶ ይደፋን? ይደፋን?
ጠላሽ ሸምጥሮ ይፍሰስን?
ይፍሰስን?
ብፈራ ነው በሰው ምላስ
ቃናሽ ኋላ እንዳይዳስ ፤
ተራርቀን እንዳንቀረው
ተመዝነን እንዳናንሰው
ብፈራ ነው እማምዬ ብጨነቅ ነው።
የሕይወትሽ ማኅደር ብራና
እንደያዘ ያንቺን ዜና
ሳይገለጥ ቀን ያልፍና
ሳይነበብ ሳይወራ ይቀርና፤
እንዳይደድቡ ዐይኖቼ
ልብ ሕሊና ጆሮቼ
የሕያው ገጽሽ ውበቱ
እንዳይነጣ ደም ግባቱ
ዐመዱ እንዳይቀር ሐውልቱ።
ብፈራ ነው እማምዬ ፡ ብጨነቅ ነው
ተራርቀን እንዳንቀረው
ተመዝነን እንዳናንሰው።

ካንቺ ርቄ - ከእኔ ርቄ
ከየምናምኑ ወድቄ
በሌላው ዕድር ጠልቄ

ልናገር ብል - ማን ሊሰማኝ?
ልጐብዝ ብል - ማን ሊያኮራኝ
እባክሽን፡ አስተምሪኝ አልተማርኩም
ጥላቻሽን ሳለመልም ፡ ፍቅርሽን ገና አላወኩም።
በአርያሽ መፈጠሬን
በለለግሽ መወሰኔን
መወለዴን ባንቺ ልደት
መቦረቄን ባንች ልጅነት
መፈንደቄን ባንች ተረት፤
- እንደምሞትም ያንቺን ሞት -
አስተምሪኝ አልተማርኩም
ጥላቻሽን ሳለመልም ፡ ፍቅርሽን ገና አላወኩም።

እማማ እማማዬ ፡
የኔነት መደብ መብቀያዬ
የኔው ቀለም አሻራዬ ፡
ነብሴን ልጣል፤ ካንቺው ጉያ - ካንቺው ገላ
ዳግም ከቶም አልሁንብሽ ተቀጥላ
የወግ ልጅ የይስሙላ።...
ቃል ኪዳኔን ትቀበይኝ
የኔ ሁኚ ፡ ያንቺ አድርጊኝ
አልለይሽ ፡ አትለኝ -
አይበድሉም ብበድልሽ
መቼም የትም እናቴ ነሽ... እናቴ ነሽ።

ገጣሚ፣ ደራሲ፣ ሃያሲና የሥነ ጽሁፍ ተመራማሪ
ደበበ ሰይፉ
የብርሀን ፍቅር የግጥም መድብሎች የተወሰደ
1964ዓ.ም.